የሰ/መ/ቁ. 60392

ታህሣሥ 26 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፣** አቶ ጌትነት የኔው - ቀረቡ

**ተጠሪ፣** አቶ ኢዩብ ቢንያም ወ/ቢኒያም ዮሐንስ - ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ሁከት ይወገድልኝ ሲል አመልካች ያቀረበውን ክስ የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎ እንደክሱ አቀራረብ ከወሰነ በኃላ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ይታገዳል ሲል መሻሩን በመቃወም አመልካች በዚህ ሰበር እንዲታረም ስላመለከተ ነው፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በድሬደዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ፍርድ ቤቱም የድሬደዋ ከተማ መሬት አስተዳደር ባለሥልጣን ስለጉዳዩ አጣርቶ መግለጫ እንዲያቀርብ ካደረገ በኃላ በዚሁ መነሻ ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ክልል ገብቶ ሁከት ፈጥሯል ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የድሬደዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ ሥር ተከሣሽ /ተጠሪ/ በአከራካሪው ይዞታ ላይ የግንብ አጥር የሰራው በ1987 ዓ.ም መሆኑን አመልካች ደግሞ ክስ ያቀረበው ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑን በማመልከት የአመልካች ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149/2/ መሠረት በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም ባሻገር በፍሬ ነገር ረገድም በይዞታ ላይ ክርክር ሲነሳ ይዞታውን በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት ባለይዞታ ቅድሚያ እንደሚሰጠው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1144/2/ ይደነግጋል በማለት ይዞታው የተጠሪ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በአመልካች በኩል የቀረበው የይዞታ ማረጋገጫ ውድቅ ተደርጐ ተጠሪ አከራካሪውን ቦታ ቀደም ሲል ይዞት ነበረ በሚል ይዞታው ለተጠሪ እንዲፀና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ህዳር 29 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል በይዘቱም አከራካሪው ይዞታ 52 ካ.ሜ የተባለው የአመልካች ይዞታ ሳይሆን ተጠሪ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በእጁ አድርጐ የሚያዝበት ስለመሆኑ በመጥቀስ አመልካች በይዞታው ሥር በሌላ ቦታ ሁከት ተፈጥሮብኛል በማለት ያቀረበው ክስ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

አመልካች ክስ ባቀረበበት ይዞታ ላይ ባለመብት ስለመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ ቁጥር 02473 መጋቢት 10 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ስለመሆኑ ይኸው ማስረጃ ሥር ፍ/ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ስለመሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ አመልካች በዚሁ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠው ይዞታ ስፋት 180 ካ.ሜ ሆኖ ከዚህ ውስጥ 52 ካ.ሜ በተጠሪ የተያዘ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡

ተጠሪ ይህንን ይዞታ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ይዠዋለሁ ይበል እንጂ የቀበሌው አስተዳደር የተጠሪ ይዞታ እና የተሰራው ግንባታ ሕገወጥ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1140 እና 1144/2/ ተጠቅሶ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት ሲታይ ተጠሪ በሕገወጥ መንገድ ይዞ በእጁ በማድረጉ ለሕገወጥ ተግባር ሕጋዊ ሽፋን እንደመስጠት ያህል መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

የፍ/ብ/ሕጉ ዓላማ በሕግ አግባብ ባለይዞታ ለሆነው ወገን ጥበቃ ለማድረግ እንጂ ሕገወጥነትን ለማበረታታት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ አግባብነት ያለው የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1146/1/ እንደሚያስገነዝበን በስውር ወይም በሚያሻማ አኳኃን የተደረገው ይዞታ ማንኛውንም መብት አይሰጥም፡፡

ስለዚህም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን ለመሻር መሠረት ያደረገው የሕግ ድንጋጌ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በዚህ አከራካሪ ይዞታ ባለመብት ስለመሆኑ በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው መጋቢት 10 ቀን 2000 ዓ.ም ሆኖ ክስ የመሠረተው ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑ ሲታይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149/2/ መሠረት የሁለት ዓመት ጊዜ አልፎበታል የሚባልበት ሁኔታ የለም፡፡

በመሆኑም አመልካች ከተጠሪ የተሻለ መብት ያለው መሆኑን ከአስተዳደር አካል የተሰጠውን የምስክር ወረቀት መሠረት አድርጐ ያቀረበው ክስ መታየት የሚገባው ይህንኑ ማስረጃ ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ እንጂ ተጠሪ በሕገወጥ መንገድ ይዞታውን በእጁ ካደረገበት ጊዜ ሊሆን አይገባም፡፡

ባጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከሕጉ ጋር በአግባቡ ሳያገናዘብ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 00514/2002 ሐምሌ 27 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የድሬዳዋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01098 ሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገው ክርክር ግራቀኙ የየራሳቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ